# ፖለቲከኛ ሲያረጅ ሰባኪ ይሆናል?

ንጋቱ ያየህ ይራድ
ዳላስ ቴክሳስ

እንዴው ትምክህተኛ ሆንክ አትበሉኝ እንጂ "ሴትኛ አዳሪ ሲያረጅ ................" የሚል የቆየ ተረት ነበር። ዛሬ ደግሞ "ፖለቲከኛ ሲያረጅ አማካሪ ይሆናል" እንደ ማለት ሰባኪ ይሆናል የሚል አዲስ ዘይቤ ተይዞ ስናይ ደግመን ደጋግመን ወዴት እየሄድን ነው? ብለን መጠየቅ ይገባናል ብዬ አምናለሁ። ዘመኑ "ገንዘብ ገንዘብ" የሚል ድክመት የጎላበት ሆኖ ሁሉም ነገር በገንዘብ መለካት ስለተጀመረም ከፖለቲካው እኩል ገንዘብ የሚካበትበት ነገር ቢኖር ሃይማኖት እየሆነ ቢመጣ የምንነረም አይመስለኝም። የፖለቲከኞቹን ሥራ በማስተዋል፡ ፖለቲካ በቃኝ ያለ ግለሰብ ለመንፈሱ እረፍት ለማግኘት ወደ ቤተክርስቲያንና መስጊድ ሲሄድ ሸሽቶት የመጣው ፖለቲከኛ እዚህም አጋፋሪ ሆኖ ሲያገኘው የቆመበትን ስፍራ እስከመጠራጠር ቢደርስ ምን ይገርማል።

ቀደም ባለ ሰዓት የተነገረ ቀልድ ለበስ ቁምነገን ላጫውታችሁ። ፊታውራሪ አሽከራቸውን ያስጠሩና ሲያናግሩት ዓይናቸውን ማየት ፈርቶ ጣራ ጣራን ይመለከታል። ፊታውራሪም በሁኔታው ተናደው ለፈጣሪ እያሳጣኸኝ ነው? አሉት አሽከራቸው በተቀላጠፈ ሁኔታ መሬት መሬት ማየት ጀመረ። አሁንም ፊታውራሪ መቀመቅ ግባ እያልከኝ ነው? ብለው ጠየቁት። አሽከራቸው በሁኔታው ተጨንቆ "ኧረ ጌታዬ ለዓይኔ ማረፊያ ስጡኝ" አለ ይሉ ነበር። ታዲያ የዘንድሮው ክስተት ኧረ ሰላሙን ስጡን የሚያሰኝ ነው። በምእራባዊው ዓለም በፖለቲካ መስክ ከተሰማሩት አብዛኛዎቹ ጠበቆች ናቸው። ታዲያ ጎበዝ ጠበቃ ማለት ጥሩ ውሸታም ማለት ነው የሚባለውን አባባል የሰማ ግለሰብ ጥሩ ፖለቲከኛ ማለት በውሸት የተካነ ማለት ነው ብሎ ቢናገር እንዴት አሌ ማለት ይቻላል?

የዛሬ ጽሑፌ መነሻ የሆነው "በትግል እሳት" ተፈትነው "በጥይት ነበልባል" መካከል አድገው በትግል የጎለመሱትንና የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትር እስከመሆን የበቁትን፡ ብሎም "ስኳር አታለላቸው" ተብሎ 12 ዓመት ዘብጥያ ወርደው አሁን ከእስራት ሲፈቱ መጽሐፍ ቅዱስ አቅፈው ሰባኪ የሆኑትን የአቶ ታምራት ላይኔን የቴሌቪዥን ቃለ መጠይቅ ሳይ የተሰማኝን ለመናገር ያክል ነው። እኔ ሰው ለምን ንስሃ ገባ አልልም። ሰው መቀየር አይችልም የሚል አመለካከትም የለኝም። ይህንን ሽፋን በማድረግ የሚነሳን ግን መለየት መቻል ያለብን ይመስለኛል። "ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል" እንዲሉ።

የቀድሞው ጠቅልይ ሚንስትር፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ "ሌባ ሌባ" ያላቸው እሳቸው ሌብነታቸውን ባደባባይ ከማመናቸው በፊት እንደ ነበር ሁላችንም የምናስታውሰው ጉዳይ ነው። ዛሬ በሃይማኖት መስበኪያ የቴሌቪዥን ጣቢያ ቀርበው "ትላንት እምነተቢስ ነበርኩ ዛሬ ክርስቶስን ተቀብዬ ባዶው ልቤ በመንፈስ ተሞልቷል" ሲሉ አዳመጥሁ። "ለመጀመሪያ ጊዜ ከእስር ቤት ወደ ሆስፒታል ለህክምና ተወስጄ በነበረበት ወቅት አንዲት ነርስ በሰጠችኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የያዘ ወረቀት አንብቤ ልቤ ተነክቶ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ተንበረከኩ፡ ጌታንም በጸሎት ለመንኩት" ይሉናል ደፋሩ ሰባኪ። አቶ ታምራት "ክርስቶስ በአካል እንደታያቸውና እንዳነጋገራቸው" ሲናገሩ እንባቸው እየጎረፈ ነበር። ንግግራቸውን በመቀጠል፡ "እስር ቤት ተመልሼ ጌታ ሆይ እንዴት እንደምጸልይ አላውቅምና እባክህ እርዳኝ ብዬ ስጸልይ አደርኩ በማግስቱ ማን እንደላከው ሳላውቅ የፀሎት መጽሐፍ እጄ ላይ ወደቀ

ይሉናል"። አቶ ታምራት ትላንት የፖለቲካ ተዋናኝ በነበሩበት ወቅት የሰበኩበት አንደበታቸው ስልጣን እንደለገሳቸው ሁሉ ዛሬም በያዙት አካሄድ ብሩህ ዘመን የታያቸው ይመስላል። ስለሆነም ከትላንትናው በተለየ መንገድ በሃይማኖት ሽፋን ሊያታልሉን ተነሱ ነው የምለው። በሌላ ቦታ ሰበካቸው ደግሞ "እስር ቤት እያለሁ ባለቤቴን በስልክ ሳናግራት እየፈራሁና እየቸርኩ "ጌታን በዚህ ቀን ተቀበልኩ" ብዬ ስነግራት እሷም ተገርማ በዚያው ቀን ከልጄ ጋር ጌታን እንደተቀበለች ነገረችኝ" ይሉናል።

ነገሩ ሆነ አልሆነ በሚል እሰጥ አገባ ለማለት ሳይሆን የተደራረበ ውሸት ነጠላ እውነትን እንደማያሸንፍ ለመጠቆም ያክል ነው። ምስክርነቱ የሚታመን ሰው የመታመን ታሪክ ያለው ነው የሚባለውን አባባል ዋጋ ውስጥ በማስገባት። እንዴው አቶ ታምራት እራሳቸውን ወደ ኋላ ቢያስተውሉ ለተና ገሩት ላደረጉት ድርጊቶች ሁሉ አእላፍ ምስክር መኖሩን ለጥንካሬአቸውና ለድክመታቸው ተጨማሪ የሚሰጥ ሕዝብ እንዳለ መዘንጋታቸው ይገርመኛል። ለአንባብያን ግንዛቤ እንዲሆን ደግሞ የበኩሌን መጠቆም እወዳለሁ።

አስራ ሁለት ዓመት በመታሰራቸው ከሚናደዱት ግለሰቦች ውስጥ አንዱ እነደሆንኩ መናገር እወዳለሁ። ለምን ብትሉኝ ከአጀማመሩ የማይችሉትን ስልጣን በመስጠታቸው መጠየቅ ያለበት የሾማቸው አካል ነው ብዬ ስለማምን። አንካሳን ውሻ አደን ይዞ ሄዶ አደን ላይ ደካማ ነው ብሎ እንደመቆጣት አይነት ስለሚያስመስል።

አቶ ታምራት ላይኔ በእስራት ዘመናቸው አልተማሩም ማለት ይከብደኛል;; እራሳቸውን የገመገሙበት ብሎም እኔ ማን ነኝ? ብለው የጠየቁበት ወቅት ለመሆኑ አልጠራጠርም። ተአምር የሰራሁበት ወቅት ነው የሚለውን ግን የበለሳን ሕዝብ እንዳታለሉት ዓይነት እንዳይሆን ቢጠንቀቁ መልካም ነው ባይ ነኝ። አቶ ታምራት "በሕይወቴ ተንበርክኬ ሳላውቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ለጌታ ከሆስፒታል አልጋዬ ወርጄ ተንበረከኩ" ብለው ሊያሳምኑን ይነሳሉ። እኔ እንደሚገባኝ ከአለቃ ጋር አብሮ መሥራትን፡ መከባበርን ሳይሆን፡ ለአመራር አባላት ማጎብደድን፤ መስገድን የጀመሩት ቀደም ባለው ሰዓት እንደነበር የሚያስታውሱ አእላፍ ታጋዮች በሕይወት እያሉ ለምን ሊዋሹን እንደተነሱ ሊገባኝ አልቻለም። አቶ ታምራት ላይኔ ሃይማኖተኛ ሆንኩ ብለው ሲነሱ ግን ብልጥ ናቸው ልጄ፡ ካሁን በኋላ ፖለቲካ እንደማያዋጣቸው ማንም ተከታይ እንደማይኖር ተገንዝበው በአዲስ ዘዴ ባዲስ መስክ የሕይወት ፍልሚያ ሊጀምሩ ነው፤ የአሁኑ ከፊተኛው የሚለየው ቢሰደቡ፤ ቢዘለፉ ይቅር ይበልህ እያሉ፤ ቢተቹና ቢነቀፉ "የተነሳህበት ይገባኛል እኔም እንዳንተ ነበርኩ" እያሉ የሚሸሸጉበት ጥሩ መጠለያ ማግኘታቸውን አውጥተውና አውርደው ነው ውሳኔ ላይ የደረሱት ብዬ ለማመን አልተቸገርኩም። ዛሬ አቶ ታምራት ላይኔ ላይ ሂስ ማቅረብ አይቻልም። እሳቸው ላይ በትላንትናው ተጸጽተው ለጌታ ያደሩ ናቸውና። ዛሬ አቶ ታምራት ላይኔ ወንጀለኛ እንደነበሩ መናገር አማኙን ታምራት ላይኔን ሳይሆን የተጠጉበትን ሃይማኖት እንደመንቀፍ ስለሚያስቆጥር። እንግዲህ "ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ከአጥር ውጭ ታሳድራለች" የሚሉት ይህንን አይነት ነገር አይተው ይመስለኛል።

አቶ ታምራት ላይኔ በእውነት ተጸጽተው ወደ መንፈሳዊ ሕይወት የገቡ ቢሆን ኖሮ ለምን ወደ እስር ቤት እነደተወረወሩ በመጸጸት ሊያወጉን በተገባ ነበር። እሳቸው ግን አድበስብሰውት ሊያልፉት ይሞክራሉ። የታሰርኩት በስልጣን ሽኩቻም ነው ሊሉን ይቃጣቸዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ እሳቸውን ሌባ ሌባ እንዳለ ሁሉ ጥሩ ስራ እየሠራ ነው የሚለውን በጊዜው ማመስገኑንም ለማስታወስ ለከንቲባ አርከበ የሰጠውን ምስክርነት በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል።

አቶ ታምራት ላይኔ በእልቅና ዘመናቸው ስንቱን እንዳልገላመጡ፡ ስንቱን በቂም ከሥራ እንዳላፈናቀሉ፡ ስንቱን የሞት ማቅ እንዳላለበሱ፡ ሁሉ እጅ ከፈንጇ ሲያዙ ፓርላማ ላይ ቀርበው ተንበርክከው መለመናቸውን እያወቅን “ተንበርክኬ አላውቅም” ማለታቸውን ሳይሆን የተንበረከኩበትንና ድርጅታቸውንም ሆነ መንግሥትን ጥፋተኛ ነኝ ብለው የተማጸኑበትን ቃላቸውን አጥፈው ዛሬ ባላጠፋሁት ተወንጅዬ ታሰርኩ ሲሉን ይቃጣቸዋል። አቶ ታምራት ኮምኒስት ነበርኩ ብለው ማመናቸው ገርሞኝ ነበር፡ ቆይቼ ሳሰበው ለሚቀጥለው የሰበካ መንገድ ጥሩ መንደርደሪያ ስለሚሰጣቸው እንጂ ባይሆን ኖሮ እሱንም ከመካድ ወደ ኋላ አይሉም ነበር። በተደጋጋሚ ሲክዱ አድምጠናልና፡፡

ለናሙና የማይረሳውን አንዳንድ ትዝታ ላንሳላቸው። በኢሕአፓ ሠራዊትና አባላት መካከል ብሎም በአመራሩ ላይ ተነስቶ  የነበረውን ችግር ለመፍታት የአመራሩን አቋም ለአባላት እንዲያስረዱ ተልከው የአባላትን መቁረጥ ሲመለከቱ ቅልብስ  ብለው ከጳጳሱ በላይ ካቶሊክ እንዲሉ የድርጅቱ ታቃዋሚ ሆነው ድርጅቱን በመልቀቅ ወደ ትግራይ ከሄደው ቡድን ጋር መረብን ተሻገሩ። በትግራይ  ቆይታቸው የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ እንቅስቃሴ የሚለው ድርጅት ሲቋቋም ከመስራች አባላት አንዱ ለመሆን እድል ገጠማቸው። በድል አድራጊነት አዲስ አበባ  ሲገባም የኢትዮጵያ ድርጅት መቀበር አለበት ሲባል አብረዋቸው ከተሰለፉት የአመራር ቡድኖች ጋር በመሆን ለመጣው ትእዛዝ ተንበርክከው አብረዋቸው የታገሉትን የደቡብ፤ የኦሮሞ፤ ጓዶቻቸውን ሜዳ ላይ አፍስሰው ዋቢና ነገረፈጅ የለውም ለተባለው የአማራው ክልል ደርጅታቸው ስሙን አስተካክሎ ከጓደኞቻቸው ጋር የአማራ ድርጅት መሆኑን አወጁ። ጓድ ታምራት እየተዘዋወሩም አማራ የበደለህ በደል ቀላል አይደለም እያሉ እወክለዋለሁ ያሉትን ብሔር በመወንጀል በሕዝብ ልብ የቂም ችግኝ  በመትከል ለብዙሃን ንጹሃን ደም መፋሰስ በር ከፈቱ። የአርሲን የሐረርን የግፍ እልቂት ያስታውሷል። የሚቃወማቸውን ለማሰር ያለተስማማቸውን ለማስገረፍ እንቢኝ ያለውን ለማስገደል ወደኋላ እንዳላሉ ፓስተር ታምራት ዛሬ ይክዱ ይሆናል። ሲክዱ ግን ተጸጽቼ ተንበረከኩ የሚሉትን አዲስ የእምነት መንገዳቸውን እየናዱ መሆኑን  መቀበል አለባቸው እላለሁ። የተጸጸተ ያደረገውን አይዋሽምና። አነሳሴ አቶ ታምራት ማን ናቸው ለመለትና ለመተረክ ሳይሆን አቶ ታምራት ባጋጠማቸው ሁሉ ሁኔታዎችን በማየት የሚቀያየሩ ለእምነት ሳይሆን  ለአለቃ ሰጋጅና ተንበርካኪ ለአላማ ሳይሆን ለግል ሕይወታዊ ጥቅም የቆሙ መሆናቸውን ለመጠቆም ያክል ነው። የፓርላማ  አባላት በተሰበሰቡበት የኢትዮጵያ ሕዝብ በቴሌቪዥን እያያቸው “ስኳር አታለለኝ” ያሉት ጠቅልይ ሚኒስትር ዛሬ ምንም ሳላጠፋ ታሰርኩ ሲሉ የምናምናቸው ከመሰላቸው ትልቅ ስህተት ተሳሳቱ እላለሁ። ለአመንኩበት ዓላማ ስታገል ነበር እንዳሉት ለዓላማ ቆመው እነደሚኮራባቸው ታጋዮች ተገርፈው፤ ታስረው፤ ተገድለው ቢሆን ኖሮ ስማቸውን እንደ አቡነ ጴጥሮስ ከሚያነሱት አንዱ ግለሰብ እሆን ነበር። ተንኮለኛ  መሆናቸውን ያየሁት ላጠፋሁት ይቅር በሉኝ  ሳይሉ፤ የበደሉኝን ጓደኞቼን እየዞርኩ ይቅርታ አደረኩላቸው ሲሉ ስሰማ ነው።

ኮሚንስቱ ክርስቲያን አቶ ታምራት ላይኔ ዛሬ የያዙት የሰበካ መንገድ እንደሚያዋጣቸው ለመገመት ምሁርነትን አይጠይቅም። “እኔም እንዲሁ አስብ ነበር፤ ከተራ ተማሪነት ጠቅላይ ሚኒስቴር ማእረግ ድረስ የደረስኩ ደረጃዬን ሳውቅ ግን ለጌታ የተንበረከኩ” እያሉ ያለፈ ወንጀላቸውን በመሸፈን መጭውን ኑሯቸውን ለማመቻቸት መነሳታቸው ከሚያበሳጨኝ የበለጠ የሚያናድደኝ ተሰብስቦ የሳቸውን ውሸት የሚያዳምጠው አድማጭ ነው። በነገራችን ላይ መንግስቱም ዛሬ የሚያዳምጠው ቢያገኝ ከስልጣን የለቀቅሁት መንፈስ በአካል ቀርቦ ካናገረኝ በኋላ ነው ሊል እኮ ነው።

አቶ ታምራት ላይኔ የትግል አጋሮቻቸውን፤ ዘመዶቻቸውን ብሎም የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲያታልሉ ቆይተዋል። ያ አልበቃ ብሏቸው ፈጣሪን ማታለል እችላለሁ ብለው ከተነሱ ግን ያሚያታልሉት እራሳቸውን ብቻ ነው።